ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ሸዕባን 8/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚኒስቴር ማርች 11/2022 ግ.

# ሰማእታትና ከፈጣሪያቸው ዘንድ ያላቸው የላቀ ደረጃ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{وَلا تَحْسَبَنَّ الَّذِينَ قُتِلُوا فِي سَبِيلِ اللهِ أَمْوَاتًا بَلْ أَحْيَاء عِندَ رَبِّهِمْ يُرْزَقُونَ * فَرِحِينَ بِمَا آتَاهُمُ اللَّهُ مِنْ فَضْلِهِ وَيَسْتَبْشِرُونَ بِالَّذِينَ لَمْ يَلْحَقُوا بِهِمْ مِنْ خَلْفِهِمْ أَلَّا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلا هُمْ يَحْزَنُونَ * يَسْتَبْشِرُونَ بِنِعْمَةٍ مِنَ اللَّهِ وَفَضْلٍ وَأَنَّ اللَّهَ لا يُضِيعُ أَجْرَ الْمُؤْمِنِينَ}

ለአለው ለኣመቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአንቀጾቹ ትርጉም፡
(እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው፡፡ በእርግጥ እነርሱ እጌታቸው ዘንድ ሕያዋን ናቸው፤ ይመገባሉ፡፡ አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ነገር ተደሳቾች ሲኾኑ (ይመገባሉ)፡፡ በነዚያም ከኋላቸው ገና በእነርሱ ባልተከተሉት በእነርሱ ላይ ፍርሃት ባለመኖሩና እነርሱም የማያዝኑ በመኾናቸው ይደሰታሉ፡፡ ከአላህ በኾነ ጸጋና ልግስና አላህም የምእምናንን ምንዳ የማያጠፉ በመኾኑ ይደሰታሉ፡፡)
አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል፡
በአላህ (ዐ.ወ.) መንገድ ሰማእት መሆን ከደረጃዎች ሁሉ የበለጠ ታላቅ ደረጃ እንድሁም ከላቁ የአላህ መቃረቢያዎች እጅግ የላቀው መቃረቢያ

ነው፡፡ ሰማእትነት እውነትን ለመጠበቅና ስለሱ ለመከላከል፣ ሀገርንና ዳር ድንበሩን እንድሁም የነዋሪዎቹን ድህንነት ለመጠበቅ በአደረባቸው ፍላጎት ሕይዎታቸውን ኣሳልፈው ለሰጡ ጅግኖች የቸረው የአለላህ (ዐ.ወ.) ምርጫ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلِيَعْلَمَ اللّهُ الَّذِينَ آمَنُوا وَ يَتَّخِذَ مِنْكُمْ شُهَدَاءَ}.

(አላህም እነዚያን ያመኑትን እንዲያውቅ (እንዲለይ) ከእናንተም ሰማዕታትን እንዲይዝ ነው፡፡)

በመሆኑም አላህ (ሱ.ወ.) ሰማእታትን በላቀ ደረጃ፣ በታላቅ ትሩፋትና ወደር በሌለው ክብር ከሌሎች ሰዎች ለይቷቸዋል፡፡ ለዚህም ከሚከተለው የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ቃል የበለጠ ማስረጃ አይኖርም፡ (መንፈሴ በእጁ በሆነችው በአላህ እምላለሁ፡፡ እኔ በአላህ መንገድ ተገድየ ከዚያም ሕያው ብሆን እንደገናም ተገድየ ሕያው ብሆን አሁንም ተገድየ ሕያው ብሆና ከዚያም ብገደል ደስ ይለኛል)፡፡

የሰማእታት ሌላው ታላቅ ደረጃ ደግሞ የሰው ልጅ አስተሳሰብ ሊደርስበት በማይችለው መልኩ ከጌታቸው ዘንድ ሕያውና የሚመገቡ መሆናቸው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلاَ تَقُولُواْ لِمَنْ يُقْتَلُ فِي سَبيلِ اللّهِ أَمْوَاتٌ بَلْ أَحْيَاء وَلَكِن لاَّ تَشْعُرُونَ}

(በአላህ መንገድ (ለሃይማኖቱ) የሚገደሉትን ሰዎችም «ሙታን ናቸው» አትበሉ፡፡ በእውነቱ ሕያዋን ናቸው፤ ግን አታውቁም፡፡)

(ከርሳቸው አላህ የውደድና) ጃቢር ኢብን አብዲላህ እንድህ ይላሉ፡ ‹አንድ ቀን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መንገድ ላይ አገኙኝና (ጃቢር ሆይ! ቀልብህ የተሰበረ ይመስለኛልሳ ምንድነው ነገሩ) ሲሉ ጠየቁኝ፡፡ እኔም የአላህ መልክተኛ ሆይ! አባቴ ልጆችና በርካታ እዳና ትቶልኝ ሰማእት ሆኖ ወደቀ አልኩኝ፡፡ እሳቸውም (አላህ አባትህን እንዴት እንደተቀበለው ላብስርህ ወይ) አሉኝ፡፡ እኔም እሺ የአላህ መልክተኛ ሆይ! አልኩኝ፡፡

እሳቸውም (አላህ (ዐ.ወ.) አንድንም ሰው ከከለላ ጀርባ ቢሆን እንጂ አናግሮ አያውቅም፡፡ አባተህንማ ሕያው አድርጎ ያለ ከለላ አናገረው) አሉኝ፡፡ በመቀጠልም እንድህ አሉ፡ (እንድህም አለው ባሪያ ሆይ! የፈለግሀውን ነገር ተመኝ እኔ እሰጥሀለሁ፡፡ እሱም ጌታዬ ሆይ! ሕያው አድርገኝና ባንተ መንገድ እንደገኛ ልገደል አለ፡፡ ጌታውመ (ዐ.ወ.) ነገሩ እንድህ ነው እነሱ ወደሷ በፍጹም አይመለሱም የሚለው ቃሌ በርግጥ ከዚህ በፊት ተፍጽሟል አለ)፡፡ ጃቢር በመቀጠል ከዚያም የምትከተለው አንቀጽ ወረደች፡፡

وَلَا تَحْسَبَنَّ الَّذِينَ قُتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ أَمْوَاتًا بَلْ أَحْيَاءٌ عِنْدَ رَبِّهِمْ يُرْزَقُونَ}

(እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው፡ ፡ በእርግጥ እነርሱ እጌታቸው ዘንድ ሕያዋን ናቸው፤ ይመገባሉ፡፡) ሰማእታት ከጌታቸው ዘንድ ሕያው እንደሆኑ ሁሉ በሀገር ማህደር ሕያው ሆነው ገድላቸው በዘመን ብዛት አይረሳም፡፡

ነፍሳቸው በጀነት እንደፈለገች በመዛወር ከጌታቸው ዘንድ የምትደሰት መሆኗ ሌላው የሰማእታት ታላቅ ደረጃ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ ይላሉ፡ (ወንድሞቻችሁ በእሁድ ጦርነት ጉዳት በደረሰባቸው ጊዜ አላህ ነፍሶቻቸው አረንጓዴ ቀለም በአላቸው አእዋፍ ሆድ አስገብቶ ወደጀነት ወንዞች እንዲወርዱ፣ ከገነት ፍራፍሬም አንዲመገቡ፣ በአርሽ ጥላ በተንጠለተሉ ከወርቅ በተሰሩ ቅንድሎች ብርሃን እንዲጠቀሙ አደረገ)፡፡

ከሰማእታት ተላላቅ ደረጃ ዎች ሌላው ደግሞ በትንሳኤ ቀን የታላቅ ምንዳና የሙሉ ብርሃን ባለቤት መሆናቸው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ وَالشُّهَدَاءُ عِنْدَ رَبِّهِمْ لَهُمْ أَجْرُهُمْ وَنُورُهُمْ}

(በጌታቸውም ዘንድ መስካሪዎቹ ናቸው፡፡ (ወይም ሰማእታትም ለእነርሱ ምንዳቸው ብርሃናቸውም አልላቸው፡፡)

ነብያችን (ሶ.ኢ.ወ.) በበድር ጦርነት ሰማእት ለሆኑት ስለልጃቸው ሓሪሳ በጠየቁ ጊዜ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ለኡም ሓሪሳ ቢን ሱራቃ እንድህ ብለዋል፡ (ኡም ሓሪሳ ሆይ! ጀነት አንድት ሳትሆን በዙ ጀነቶች ናቸው ለጅሽ የላይኛውን ፊርደውስ አግኝቷል)፡፡

በመልካም ሁኔታ ሰላሳደጓቸውና ስለአዘጋጇቸው በትንሳኤ ቀን ለቤተሰቦቻቸው ታዳጊ መሆናቸው ሌላው የሰማእታት ትሩፋት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሰማእት በትንሳኤ ቀን ከቤተሰቦቹ ሰባ ለሚሆኑት ታዳጊ ይሆናል)፡፡

ሌላው የሰማእት ታላቅ ደረጃ ደግሞ ምንዳቸው የማይቋረጥ፣ ይልቁንም ምሉእና እጥፍ ድርብ ሆኖ የሚቀጥል መሆኑ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ማንኛውም ሰው በሞተበት ሰኣት በነበረበት የአላህ መንገድ ሥራው ይደመደምለታል እስከ እለተ ቂያማ ድረሰም እንዲለማ ይደረግለታል፡፡ ከመቃበር ፈተናም ይድናል)፡፡

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልከተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

የሰማእት የላቅ ደረጃን የሚያገኘው እውነትን የአወቀ ለሱም ታማኝ የሆኑ ስለሱ የተከላከለና ለሱም መስዋእትነት የከፈለ እውነትኛ ሰማእት መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡ እውነተኛ ሰማእት ያ ምድሩን፣ ክብሩን፣ ሀገሩንና የቤተሰቡን ደህንነት ሲከላከል የሞተ ሰው ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ገንዘቡን ሲከላከል የተገደለ ሰማእት ነው፡፡ ቤተሰቡን ወይም ሕይወቱን ወይም ሃይማኖቱን ሲከላከል የተገደለም ሰማእት ነው)፡፡

እዚህ ላይ እኛ ልናረጋግጥ የምንፈለገው ነገር አለ፡፡ እሱም ለሰማእቶቻችን ነፍስ ታማኝ የምንሆነው በተለያዩ መስኮች ለዚህ ታላቅ

ሀገር ጠባቂ ወታደር ስንሆን እሱንም ለማገልገል ለእያንዳንዳችን የተቻለንን ሁሉ ስናደርግ እንድሁም ከጦር ሃይላችን፣ ከፖሊስ ተቋማትና ከሌሎችም ብሄራዊ ድርጅቶች ጎን ከአላህ ዘንድ የሰማእትን መንዳ በመጠበቅ በአንድ ልብና በአንድ ዓይነት ስሜት ስንቆም ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያለብን መሆኑን ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከልቡ ሰማእትነትን የለመነ ሰው ከአልጋው ላይ ቢሞትም እንኳ አላህ የሰማእትነትን ደረጃ ይቸረዋል)፡፡

ጌታችን ሆይ! ሀገራችን ግብጽንና ሌሎችንም የዓለም ሀገራት ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን፡፡ አሚን፡፡